# ቤተሰቤን ለሮኬት ተኩስ ስጋት ማዘጋጀት

ውድ ነዋሪ

ከጋዛ ሰርጥ ሊወነጨፉ በሚችሉት የሮኬት ጥቃቶች ሳቢያ ቤተሰብዎ ይህን ስጋት መቋቋም እንዲችል ማሰልጠንዎ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ቀደም ብሎ የሚደረግ ዝግጅት የቤተሰብዎን የደህንነት ስሜት ከማሻሻሉም በተጨማሪ አደጋው በሚከሰትበት ጊዜ ሕይወታቸውን ሊያተርፍላቸው ይችላል፡፡ ባለፈው ዓመት ውስጥ ለአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታዎች ስለመዘጋጀት የሚገልጹ በርካታ መረጃ አዘል ጽሑፎችን አግኝተዋል፡፡ ይህ ጽሑፍ ደግሞ የሚወነጨፉ ሮኬቶች የሚፈጥሩትን ስጋት መቋቋም እንዲችሉ ይረዳዎታል፡፡ በመሆኑም ለዝግጅት የሚረዱትን አስፈላጊ እርምጃዎች መውሰድዎ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ለወላጆችም ሆነ ለልጆች ችግሩን በመቋቋም ረገድ ዋናው የእርዳታ ምንጭ ቤተሰብ መሆኑ የታወቀ ሐቅ ስለሆነ ሁሉም የቤተሰብ አባላት በዝግጅቱ መሳተፋቸውና ሊነሳ የሚችለውን ሁኔታ በሚገባ ለመቋቋም የሚያስችሉትን ቁሳቁሶች ማግኘታቸው ወሳኝ ነው፡፡

እኛም ከጎንዎ ነን፡፡

ሆም ፍሮንት ኮማንድ

## መሸሸጊያ ክፍል መምረጥ የሚቻልበት መንገድ

በሚከተሉት ነጥቦች መሠረት በቤትዎ ወይም በሚገኙበት በማንኛውም ቦታ መሸሸጊያ ቦታ መምረጥዎ በጣም አስፈላጊ ነው፡-

1. MAMAD – "የመኖሪያ ቦታ መሸሸጊያ"ን የሚወክል የዕብራይስጥ ምኅጻረ ቃል ወይም MAMAK – "የሕንጻ ውስጥ መሸሸጊያ"ን የሚወክል የዕብራይስጥ ምኅጻረ ቃል
2. ባሉበት ሕንጻ ውስጥ MAMAD ወይም MAMAK ከሌለ የሮኬቱ ስጋት ካለበት አቅጣጫ የተቻለውን ያህል ርቆ የሚገኝ መሸሸጊያ ክፍል ይምረጡ፡፡ ክፍሉ ቢያንስ አንድ ተጨማሪ የውጭ ግድግዳ፣ መስኮትና ክፍተት ያለው ቢሆን ይመረጣል፡፡ እንዲህ ዓይነት ክፍል ካልተገኘ የደረጃውን ሥር መሸሸጊያ ቦታ አድርገው ሊመርጡ ይችላሉ፡፡
3. MAMAD የሌለበት የላይኛው ደርብ ነዋሪዎች ከመኖሪያቸው አንድ ፎቅ ወርዶ የሚገኘውን የደረጃ ሥር እንደ መሸሸጊያ ቦታ መምረጥ ይኖርባቸዋል፡፡

## በሮኬት ተኩስ ወቅት ልናሳየው የሚገባውን ባሕርይ የሚመለከት መመሪያ

የማስጠንቀቂያው ድምጽ ሲሰማ ወይም የፍንዳታ ድምጽ ሲሰሙ ወይም "የቀይ ቀለም" ማንቂያውን ሲያዩ በ15 ሰከንድ ጊዜ ውስጥ የሚከተሉትን መመሪያዎች መተግበር ይኖርብዎታል፡-

<u>ቤት ውስጥ ከሆኑ</u> ወዲያውኑ MAMAD ውስጥ ይግቡና የብረት መስኮቱን ይዝጉ፡፡ ቤቱ ውስጥ MAMAD ከሌለ አደጋው ከሚመጣበት አቅጣጫ በተቃራኒ ጥግ ወደሚገኘው ክፍል ይግቡ፡፡ ክፍሉ ቢያንስ አንድ ተጨማሪ የውጭ ግድግዳ፣ መስኮትና ክፍተት ያለው ቢሆን ይመረጣል፡፡ እንዲህ ዓይነት ክፍል ካልተገኘ ወደ ደረጃው ሥር ይግቡ፡፡

<u>ከቤት ውጭ ከሆኑ፡-</u> የተገነቡ ቤቶች ባሉበት አካባቢ በአቅራቢያዎ ወደሚገኘው ሕንጻ ወይም መጠለያ ይግቡ፡፡ ገላጣ በሆነ አካባቢ ከሆኑ ደግሞ በሆድዎ ይተኙና ጭንቅላትዎን በእጆችዎ ይከልሉ፡፡

<u>በተሽከርካሪ እየተጓዙ ከሆነ</u> ወደ ጥግ ወጥተው ይቁሙና ከተሽከርካሪው ወጥተው በቅርብ ወደሚገኘው ሕንጻ ወይም መጠለያ ይግቡ፡፡ ገላጣ በሆነ አካባቢ ከሆኑ ደግሞ ይተኙና ጭንቅላትዎን በእጆችዎ ይከልሉ፡፡

<u>ከ5 ደቂቃ በኋላ</u> ሌላ መመሪያ ካልተሰጠ በቀር መሸሸጊያውን ለቅቀው መውጣት ይችላሉ፡፡